# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
# 2024–2025 CAFETERIA NEWS & MEALS INFORMATION
# የካፍቴሪያ ዘገባ እና የምግብ ዝርዝር መረጃ

**ልጆች ለመማር ጤናማ ምግብ ያስፈልጋቸዋል።** የምግብ እና የተመጣጠነ አመጋገብ አገልግሎት ክፍል በየዓመቱ ከ18 ሚሊዮን በላይ ምግቦችን ያቀርባል። ለተማሪዎች ጤናማ የምግብ አማራጮችን እናዘጋጃለን፥ እንዲሁም አልሚ ምግቦች በተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነት እንዲኖራቸው ለማሻሻል በተከታታይ አዳዲስ መንገዶችን እንቀይሳለን።

በትምህርት ቤት ካፊቴሪያ ላልተከፈለ የተማሪዎቻቸው ሂሳብ ወላጆች/አሳዳጊዎች ሀላፊነት አለባቸው)። ክፍያ የሚፈፀመው በጥሬ ገንዘብ፣ ወይም ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካፊቴሪያ አካውንት ምግብ በሚገዙበት ጊዜ ወይም በማንኛውም ጊዜ ኦንላይን የቅድመ ክፍያ ስርዓት በመከተል ነው። ካፍቴሪያዉ እንደሁኔታው የሚያገለግል እና አመቺነት ያለዉ በኮምፒውተር የታገዘ የገንዘብ ክፍያ ስርዓት ይከተላል። በካፍቴሪያ አካውንት ገንዘብ ማስቀመጥ ልጆች በየቀኑ ገንዘብ ይዞ/ይዛ መመላለስን ያስወግዳል። **ሁሉም ተማሪዎች አካውንታቸውን ለመጠቀም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ መለያ ቁጥራቸውን ይጠቀማሉ** (የትምህርት ቤት ክፍቴሪያዎች በሚያስከፍሉበት ጊዜ በተማሪ መታወቂያ ካርዶች ላይ የሚገኘውን ባርኮድ ወይም የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የምግብ ካርዶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ)። ካለፈው የትምህርት አመት በተማሪ ሂሳብ ላይ የተረፈ ማንኛውንም ገንዘብ ካለ ለክፍያ መጠቀም ይቻላል። ት/ቤት ከመጀመሩ አስቀድሞ በተማሪ አካውንት ላይ የቅድሚያ ክፍያ መፈፀም ይቻላል።

**ቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም፡-**

- MySchoolBucks.com በክሬዲት ካርድ ቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም የኦንላይን አገልግሎት ይጠቀሙ። ወላጆች የምግብ አካውንት ሂሳባቸውን ለመፈተሽ፣ ተደጋጋሚ ክፍያዎችን ለመፈፀም፣ እና ለሌላም ተጨማሪ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። ለመመዝገብ ይህንን MySchoolBucks.com **በይነመረብ ይክፈቱ።**
- ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ ይሙሉ እና ለካፊቴሪያ የሚከፈል ቼክ ወይም የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ ይጨምሩበት። ስለቼክ ክፍያ ፖሊሲ ከዚህ በታች ያለውን መመሪያ ይመልከቱ።

**ከአሁን በኋላ MCPS ላልተመዘገበ ተማሪ ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም የቀሪ ሂሳብ ማስተላለፍን ለመጠየቅ፣ DFNHelpDesk@mcpsmd.org ኢሜይል ያድርጉ**

**ስለ ቼክ ተቀባይነት ፖሊሲ፡-** ለምግብ የሚከፈል ቼክ፡- ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የተማሪ መታወቂያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል ቼክ ባንኩ ሳይቀበል ተመላሽ ከተደረገ ለተከሰተው ወጭ ማካካሻ ይዳረጋሉ። የሜሪላንድ ስቴት በኤሌክትሮኒክስ ዴቢት ወይም ድራፍት የሚከፈል $25 የማካካሻ ክፍያ ይፈቅዳል። እርስዎ በቼክ ሲከፍሉ እነኝህን መመሪያዎች ማወቅዎን እና መቀበልዎን ማረጋገጥ አለብዎት። ስለ እኛ የቼክ አቀባበል ፖሊሲ ማናቸውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ CHECKredi at 1-800-239-1222 ይደውሉ።

### MCPS የምግብ ፖሊሲ

*ፖሊሲ JPH የምግብ እና የአልሚ ምግብ አገልግሎት ፕሮግራም* በሞንትጎመሪ ካውንቲ በልጅነት እድሜ የረሃብ ችግር የሚያጋጥማቸውን ለመርዳት ጥረት የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን፣ የምግብ ክፍያ ሂደቶችን፣ እና ተማሪዎች በካፊቴሪያ ያለባቸውን ቀሪ ሂሳቦች የሚከፍሉበትን አሠራር ይዘረዝራል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ድረገጻችንን ይጎብኙ

*ይህ ተቋም በእኩልነት የሚያገለግል ድርጅት ነው።*

### የምግብ ዋጋ

- **ቁርስ ምግብ $1.30**
- **የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምሳ ምግብ $2.55**
- **የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምሳ ምግብ $2.80**

*በሜሪላንድ ለቅናሽ ምግብ የተፈቀደላቸው ልጆች የምግብ ወጪ አይከፍሉም።*

**ከቁርስ እና ምሳ በተጨማሪ በግዢ የሚቀርቡ "A LA CARTE FOODS AND BEVERAGES" ምግቦች እና መጠጦች ይኖራሉ።**

በተማሪዎ ት/ቤት ካፍቴሪያ የተለያዩ ከምግብ ዝርዝር ላይ የሚታዘዙ እና የሚከፈልባቸው ምግቦች/a la carte items ይኖራሉ። ለሽያጭ የሚቀርቡ ነገሮች ሁሉም JPG-RA *ይከተላሉ። ስለ መልካም ጤንነት፡- አካላዊ እና ጤናማ አመጋገብ* በእያንዳንዱ ት/ቤት የተወሰኑ ነገሮች/items ይለያያሉ። በልጅዎ ት/ቤት ስለሚገኙ ነገሮች ወይም ከምግብ ዝርዝር ላይ ብቻቸውን የሚታዘዙ እና የሚከፈልባቸው ምግቦችን "a la carte items" የግዢ መጠን ለመገደብ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎ የት/ቤትዎን ካፍቴሪያ ማናጀር ያነጋግሩ።

### የነፃ እና የቅናሽ - ዋጋ ምግብ ማመልከቻ

የፌደራል የገቢ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ቤተሰቦች በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ የምግብ ተጠቃሚነት ብቃት ይኖራቸዋል። ለሁሉም ልጆች ሚስጥራዊነቱ እንዲጠበቅ እና ማንም ልጅ በነጻ ወይም በቅናሽ ዋጋ ምግብ እንደሚቀበል በግልፅ እንዳይታወቅ የተማሪ መታወቂያ ቁጥራቸውን ይጠቀማሉ። ቤተሰቦች MySchoolApps.com **በኦንላይን ሲያመለክቱ የማከናወኛ ጊዜው በከፍተኛ ሁኔታ ስላጠረ በይነመረብ ላይ እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።** የወረቀት ማመልከቻ ከፈለጉ ከልጅዎ ትምህርት ቤት ሊጠይቁ ይችላሉ። በአንድ ቤተሰብ ለሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች የሚያስፈልገው አንድ ማመልከቻ ብቻ ነው። በየዓመቱ አዲስ ማመልከቻ መሞላት አለበት

### የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን አገናኝ/ሊንክ ይመልከቱ፡-

- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/food-and-nutrition (የምግብ ዝርዝር፣ የአመጋገብ መረጃ እና ሌሎችንም ይመልከቱ)
- www.MySchoolBucks.com (የምግብ ሂሳብ ቅድመ ክፍያ ለመፈጸም፣ በአካውንት ያለውን የሂሳብ ሚዛን ለማየት እና የክፍያ ሁኔታዎችን ይመልከቱ)
- www.MySchoolApps.com
  (apply for Free or Reduced-price Meals (FARMS))
  (ለነጻ ወይም ለቅናሽ ዋጋ ምግብ (FARMS) ያመልከቱ)
- **1-800-332-6347 ይደውሉ ወይም** https://dhs.maryland.gov/ ይጎብኙ
  (ተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፣ ጊዜያዊ የገንዘብ ድጋፍ (TCA)፣ የሴቶች፣ የጨቅላ ህጻናት እና የልጆች ፕሮግራም (WIC) እና የህክምና ፕሮግራሞች መረጃ)

---

### የቅድሚያ ክፍያ ቅጽ

እባክዎ ቼኩ ላይ ለልጅዎ ት/ቤት ካፍቴሪያ የሚከፈል ብለው ይጻፉበት (ለምሳሌ፡- Arcola Elementary Cafeteria). ለት/ቤት ምግቦች ለመክፈል የሚጠቀሙባቸው ቼኮች ላይ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር እንዲኖርባቸው ያስፈልጋል። እባክዎን የልጅዎን የመጀመሪያ ስም፣ የአያት ስም እና የተማሪ መታወቂያ ቁጥር በቼኩ ፊት ለፊት ላይ ይጻፉ። ይህ ቼክ ለካፍቴሪያ ክፍያ/ግዢ ብቻ ነው። እባክዎን እያንዳንዱን ተማሪ በተለይ በመመዝገብ ክፍያውን ለካፍቴሪያ ማናጀር ያቅርቡ። እናመሰግናለን!

የተማሪ ስም ____________________ የመታወቂያ ቁጥር ____________ መጠን $ ____________

የተማሪ ስም ____________________ የመታወቂያ ቁጥር ____________ መጠን $ ____________

የተማሪ ስም ____________________ የመታወቂያ ቁጥር ____________ መጠን $ ____________

የወላጅ/የሞግዚት ስም ______________________________ የስልክ ቁጥር ______________